ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies(FSS)

መጋቢት 2015 | የፖሊሲ ፍሬ ኃሳቦች | ቁጥር 46

# የሴት ቅጥር ሠራተኞች የሥራ ሁኔታ እና ለውጦች በኢትዮጲያ ፦ አዲስ አበባ ውስጥ ካሉ ካፌ እና ሬስቶራንቶች የተገኙ ተሞክሮዎች

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ ነክ ምርምሮችን የሚያካሂድ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው።

♣ ♣ ♣

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

♣ ♣ ♣

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፤ በልማት ዙሪያ ውይይቶችንም ያካሂዳል።

♣ ♣ ♣

በርዕሱ ዙሪያ ኃሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜል አድራሻችን ላኩልን።

♣ ♣ ♣

ኢሜል፡ fss@ethionet.et

ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org

## መግቢያ

በኢትዮጵያ የሴቶች የሥራ ስምሪት መጠን እና የሰው ሃይል ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ ሲሆን በሴቶች ላይ ያለው የሥራ አጥነት መጠን በከተሞች በጣም ከፍ ያለ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት የተለያዮ እቅዶችን በመንደፍ፣ ፖሊሲዎችን በማሻሻል ስራ የሚፈጥሩ አካላትን በማበረታታት፣ ሁሉን አቀፍ የሆኑ ድጋፍ ሰጪ ውይይቶች እና የተለያዩ አዎንታዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ይሁን እንጂ የሥራ አጥነት ሁኔታ አሁንም እንደቀጠለ ሲሆን የሴቶች ሥራአጥነት ደግሞ ይበልጡን እየተባባሰ ሄዷል። በዚህም የተነሳ የሴቶችን እና የወጣቶችን የሥራ እድል ማስፋፋት የመንግስት ዋነኛ እቅድ ሆኖ ቀጥሏል። በዚህም መሠረት በቱሪዝሙ መስክ የአገልግሎት ጥራትን ማሻሻል እና ብቁ የስራ ሀይልን አቅም መገንባት እና ማፍራት የ10 ዓመቱ የልማት አቅድ (2021-2030) ዋነኛ ትኩረት ነው።

በተጨማሪም በቅርቡ የተሻሻለው የኢትዮጵያ የሠራተኛ ሕግ (አዋጅ ቁጥር 1156/2019) የሴቶችን የሥራ ሁኔታ በሚመለከት (አንቀጽ 87) ሴቶችን በጾታ ላይ የተመሠረተ አድልዎ እንዳይደርስባቸው መከላከልን የሚያስችሉ ህጎችን ደንግጓል፣ በተመሳሳይም፣ የአስር ዓመቱ የእድገት እቅድ (2021-2030) የሴቶችን አጠቃላይ አቅም ግንባታን ለማጎልበት እና በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ላይ የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለማመቻቸት ያለሙ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል። በጥቅሉ ሲታይ እቅዱ የሴቶችን ደህንነትና መብት ማስጠበቅ፣ በኢኮኖሚ ልማት ተሳትፏቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ከአካላዊ፣ ከጾታዊ እና ከስነልቦናዊ ጥቃቶች ነፃ የሆኑ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርን ያጠቃልላል።

የሆቴል እና ቱሪዝም ዘርፍ ለ2. 2 ሚሊየን ዜጎች የሥራ እድል የፈጠረ ነው። በሌላ አነጋገር በኢትዮጵያ ካለው አጠቃላይ የሥራ እድል 8.3 በመቶ የሚሆነውን የማህበረሰብ ክፍል የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ያደረገ ነው። ይሁን እንጂ በዘርፉ የተቀጠሩ ሴቶች መብትና ጥቅም እስካሁን በተገቢው ደረጃ አልተከበረም። በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሴቶች ወሲባዊ እና ስነልቦናዊ ጥቃቶችን ጨምሮ ምቹ ላልሆነ የሥራ ሁኔታ ይጋለጣሉ። በአጠቃላይ ዘርፉ በርካታ ተግዳሮቶች ያሉበት ነው። የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ በቂ ያልሆነ ክፍያ እና ጥቅማጥቅሞች፣ ዝቅተኛ የአገልግሎት የጥራት ደረጃ እና ዝቅተኛ የደንበኛ እርካታ በዘርፉ ከሚስተዋሉት ችግሮች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

የዚህ አጭር መግለጫ አጠቃላይ ግብ በአዲስ አበባ ካፌዎች እና ሬስቶራንቶች ውስጥ ያሉ አስተናጋጆች የስራ ሁኔታ ማሳየት ነው። ይህም የማኅበራዊ እና ስነ-ሕዝብ ባህሪያትን፥ የመደራደር አቅምን፥ ገቢን፥ ጥቅማጥቅሞችን እና የሴት አስተናጋጆችን የሥራ ሁኔታ በመገምገም ተግዳሮቶችን ለመቋቋም የሚረዱ ምክሮችን በአጭሩ ያቀርባል።

## የጥናቱ ዘዴ

በአዲስ አበባ መስተዳድር ሶስት ክ/ከተሞች (አራዳ፣ ቂርቆስ እና ቦሌ) በሚገኙ በመስተንግዶ ዘርፍ ያሉ አስተናጋጆች በጥንቃቄ ተመርጠዋል። ጥናቱ በዋነኝነት የተመሠረተው ከ270 አስተናጋጆች ጋር በተደረገ  ቃለ-መጠይቅ ከተሰበሰበ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ላይ ነው። የተመረጡት ክ/ከተሞች ከፍተኛ የካፌዎች እና ሬስቶራንቶች ቁጥር ያላቸው ናቸው። በየክ/ከተማው ከሚገኙ አስተናጋጆች ጋር በሶስት ምድብ የተከፈለ የቡድን ውይይትም ተካሄዷል። በተጨማሪም ከካፌዎቹ እና ሬስቶራንቶቹ አስተዳዳሪዎች እና ሱፐርቫይዘሮች እንዲሁም ከሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሰራ ኃላፊዎች ጋር ጥልቅ ቃለ ምልልስ ተደርጓል። የሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች እና ልዩ ልዩ ጥናቶች ፍተሻም የጥናቱ አካል ነበር። የመስክ መረጃ ስብሰባው የተካሄደው በሰኔ ወር 2014 የመጀመሪያ ሳምንታት ላይ ነው።

## የጥናቱ ቁልፍ ግኝቶች

በአዲስ አበባ በሚገኙ ካፌዎች እና ሬስቶራንቶች ውስጥ ያሉ አስተናጋጆች በአብዛኛው ወጣት ስደተኞች ሲሆኑ እነዚህም በዋናነት ከአማራ፣ ኦሮሚያ እና ደቡብ ክልል ገጠራማ አካባቢዎች የመጡ ናቸው። በአብዛኛው ያላገቡ ሲሆኑ በእነሱ ጥገኛ የሆኑ የቤተሰብ አባላት ያሏቸው ናቸው። አብዛኞቹ አስተናጋጆች ገና በወጣትነት እድሜ ክልል  ያሉ ሲሆኑ ወደ አዲስ አበባ የተሰደዱት በዋናነት የሥራ እና የተሻለ ትምህርት ዕድል ፍለጋ ነው። የተወሰኑት ደግሞ ከተማው ውስጥ ከሚኖሩ ዘመዶቻቸው ጋር ለመኖር የመጡ ናቸው። ከአስተናጋጆቹ ውስጥ ወደ አንድ-አራተኛ (¼ኛ) የሚጠጉት የሁለተኛ ደረጃ ወይም ከዚያ ከፍ ያለ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ ከሆቴል አገልግሎት ጋር የተያያዘ የሙያ ስልጠና የወሰዱ ናቸው። በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ካፌዎች እና ሬስቶራንቶች ውስጥ ከሚሰሩት  አስተናጋጆች ውስጥ ሩብ ያህሉ በዘርፉ ከአንድ ዓመት በላይ በስራው ላይ ያልቆዩ ተቀጣሪዎች ናቸው።

አሁን ባሉት የቅጥር አሠራሮች መሠረት የሥራ ልምድ እና ክህሎት አስተናጋጅ ለሚቀጥሩ ተቋማት በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚቀመጡ መስፈርቶች ናቸው፡፡ ይልቁንም በአንደኛ ደረጃ ወጣትነት፣ አጠቃላይ አካላዊ ውበት እና የተቋሙን የአለባበስ ህግጋት ለመከተል ፈቃደኛ መሆን የካፌዎችና ሬስቶራንቶች አስተዳዳሪዎች እና ባለቤቶች አስተናጋጆችን በሚቀጠሩበት ወቅት ቅድሚያ የሚሰጧቸው መስፈርቶች ናቸው።

የሥራቸው ባህሪ ለአካላዊ እና አእምሮአዊ ጫና የሚዳርግ ቢሆንም የሴት አስተናጋጆች ደመወዝ በሁሉም መለኪያ ዝቅተኛ ነው። ይህም በመሆኑ ሴት አስተናጋጆች አብዛኛውን ገቢያቸውን የሚያገኙት ከመደበኛ ደመወዝ ሳይሆን ደንበኞች በሚተዉላቸው የአግልግሎት ጉርሻ (ቲፕ) ነው ። የሴት አስተናጋጆች አማካይ ገቢ 3254 ብር ሲሆን፥ ከዚህ ውስጥ 951 ብር (28%) ብቻ ከደመወዝ፥ 1956 ብር (60%) ከጉርሻ (ቲፕ) ይገኛል። የጥናቱ ግኝት ከደንበኞች የተሻለ ቲፕ የሚያገኙት ከፍ ያለ ትምህርት ደረጃ ያላቸው፥ በወጣትነት እድሜ ክልል ላይ ያሉ፥ የአዲስ አበባ ተወላጆች፥ እና በቀን ውስጥ ለተወሰኑ ሰዓታት ብቻ የሚሰሩ አስተናጋጆች እንደሆኑ አመላክቷል።

ለአብዛኞዎቹ ዝቅተኛ ክፍያ በሚከፈልባቸው ስራዎች ውስጥ ላሉ ሠራተኞች ገንዘብ-ነክ ያልሆኑ ማበረታቻዎች እና ጥቅማ-ጥቅሞች ከመደበኛ ደሞዝ ባልተናነሰ ሁኔታ ሠራተኞችን ያነሳሳቸዋል። ሆኖም፣ በጥናቱ ውጤት መሠረት፣ አብዛኞዎቹ አስተናጋጆች እንደ ማበረታቻ የሚያገኙት ዋነኛው ጥቅም ምግብ ብቻ ነው። በጣም ጥቂቶቹ እንደ መኖሪያ ቤት፣ መጓጓዣ፣ የህክምና ወጪ ፣ ትምህርት እና ስልጠና የመሳሰሉ ጥቅሞችን እንዳገኙ በጥናቱ ተመላክቷል።

የኑሮ ወጪን በተመለከተ ምግብ፥ የቤት ኪራይ እና ቤተሰብን መደገፍ በአስተናጋጆች ኑሮ ላይ ታላቅ የሚባል ጫና ያላቸው ወጪዎች ናቸው፤ ትራንስፖርት፥ የአየር ሰዓት፥ የጤና እንክብካቤ እና ትምህርትም ቀላል የማይባል የወጪ ድርሻ አላቸው።

ምንም እንኳን የኢትዮጵያ የአሠሪና ሠራተኛ ህግ ቀጣሪዎች ከሠራተኛው ጋር የኮንትራት ውል እንዲፈርሙ ወይም በጠየቁ ጊዜ ሁሉ የስራ ልምድ ደብዳቤ እንዲሰጣቸው ግዴታ ቢጥልም፣ በካፌ እና ሬስቶራንት ውስጥ ከሚገኙት አስተናጋጆች ከሁለት ሶስተኛው በላይ የሚሆኑት የሚቀጠሩት በመንደር ደላሎች በኩል ነው። የሚሰጣቸው የቅጥር ደብዳቤም የለም። የቅጥር ውልም አይፈርሙም። አስተናጋጆች ተቋማቱን ለቀው ሲወጡም ቢሆን አብዛኞዎቹ ካፌዎች እና ሬስቶራንቶች ለሰራተኞቻቸው የስራ ልምድ ማስረጃም አይሰጡም።

አብዛኞዎቹ ሴት አስተናጋጆችም በሚሰሩበት ድርጅት ውስጥ በቋሚነት መቀጠርን አይፈልጉም፡፡ የበለጠ ትርፋማ አማራጮችን ለማግኘት ሲሉ ውል

አለመዋዋልን ይመርጣሉ። አስተናጋጆች በአንድ ተቋም ውስጥ የሚኖራቸው የተራዘመ ቆይታ በአጠቃላይ በሚያገኙት ጥቅማ-ጥቅም (ቲፕ) መጠን ላይ ይወሰናል፣ ይህም የሆነው አብዛኛው ገቢያቸው በቲፕ መልክ የሚገኝ ስለሆነ ነው ።

በካፌና ሬስቶራንቶች ውስጥ የተቋቋሙ የሠራተኛ ማኅበራትን ማግኘት ብዙም ያልተለመደ ነው፣ የሠራተኛ ማኅበራት ኃላፊዎች ሠራተኞች በማህበር እንዳይደራጁ እንቅፋት የሚፈጥሩ ካፌዎች እና ሬስቶራንቶች እንዳሉ ተናግረዋል። ይልቁንም ሴት አስተናጋጆች እንደ እቁብ የመሰሰሉ መደበኛ ያልሆኑ ኢ-መደበኛ ተቋማትን በመጠቀም እንደ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ ሠርግ፣ ወዘተ ባሉ አጋጣሚዎች እርስ በእርስ ለመደጋገፍ እና ሌሎች የግል ችግሮቻቸውን ለመፍታት ይሞክራሉ።

የሠራተኛ ጉዳይ ይመለከታቸዋል የሚባሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በካፌ እና ሬስቶራንቶች ላይ በቂ ቁጥጥር እና ክትትል አያደርጉም። ግኝቶቹ እንደሚያሳዩት ከሬስቶራንቱ ወይም ካፌው ስራ አስኪያጅ ወይም ከሌሎች ሠራተኞች ጋር የሚፈጠር አለመግባባት፣ የእድሜ መግፋት እና የክብደት መጨመር ወደ መባረር እና የስራ ውልን እስከ ማቋረጥ ሊያደርስ ይችላል።

ሴት አስተናጋጆችን ከሚገጥሟቸው መሰናክሎች መካከል፣ የስራው አጠቃላይ ባህሪ፣ ከባልደረቦቻቸው ጋር በሚፈጠር ግጭት ምክንያትያላቸው ግንኙነት መሻከር፣ ማህበረሰባዊ ብሂሎች እና ሃላፊነቶች፣ መድልዎ፣ የሠራተኝነት መብትን መነፈግ፤ አነስተኛ ደሞዝ፣ የጥቅማ ጥቅሞች እና የሥራ እድገት እድል አለመኖር ፣ እና የተለያዩ አይነት ፆታዊ ትንኮሳዎች ናቸው። ካፌዎችን እና ሬስቶራንቶችን በማስተዳደር ላይ የተሰማሩት በአብዛኛው ወንዶች ሲሆኑ ሴት አስተናጋጆቹ ላይ አልፎ አልፎ ወሲባዊ ትንኮሳ እና አካላዊ ጥቃትን እንደሚያደርሱ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ሴት አስተናጋጆችን የሚገጥሙዋቸው አስቸጋሪ ፈተናዎች እና የህይወት መሰናክሎች በስራቸው ካሉት ጥገኛ የቤተሰብ አባላት ብዛት ጋርም ይያያዛል። ይህ ሁኔታ ከሌላ አካባቢ ተሰደው በመጡና ለረጅም ጊዜ በመስተንግዶ ሥራ ላይ በቆዮ ሴት አስተናጋጆች ላይ ጫናው የበለጠ ነው።

## የፖሊሲ ምክረ-ሃሳቦች

**የሠራተኛ ማሕበራት መመስረት**፡-የሠራተኛ ማሕበራት ሠራተኞች ምቹ የሥራ ሁኔታ እንዲኖራቸውና በጥቅማ ጥቅሞች ዙሪያ የመደራደር አቅም እንዲኖራቸው እንደሚያግዝ ይታመናል። ነገር ግን በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ አነስተኛና መካከለኛ ካፌ እና ሬስቶራንቶች ውስጥ አስተናጋጆችን ያቀፈ የሠራተኞች ማሕበር ያልተለመደ ነው። የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማሕበራት ኮንፌዴሬሽንና የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በጋራ በመሆን ለሠራተኛ ማሕበራት ምስረታ አጋዥ የሚሆን የፖሊሲ ማዕቀፍና መመሪያ ማዘጋጀት አለባቸው።

**ክትትል**፡-በአዲስ አበባ በሚገኙ አነስተኛና መካከለኛ ካፌ እና ሬስቶራንቶች ውስጥ ያለው የሠራተኛና አሠሪ ግንኙነት ዙሪያ የሚደረግ ክትትል የለም ወይም አነስተኛ ነው። የሠራተኛ ማሕበራት ኮንፌዴሬሽንና የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በአነስተኛ ካፌዎች እና ሬስቶራንቶች ውስጥ የሚደረግን ክትትል ማጠናከር አለባቸው።

**አቅም ግንባታ**፡- ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ አነስተኛ ሆቴሎች፣ ካፌዎች እና ሬስቶራንቶች ያለው ዝቅተኛ የጥራት ደረጃ እና የአገልግሎት ጥራት ማነስ በዘርፉ እድገት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እያሳደረ ሲሆን ችግሩ አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰ ነው። ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት - በዋናነት ባህልና ቱሪዝም፣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ፣ ንግድ ቢሮ፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና የስልጠና እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአስተናጋጆችን አቅም በስልጠና እና በክትትል ማሻሻል አለባቸው።

**ደሞዝ፡-** የካፌዎች እና ሬስቶራንቶች አስተናጋጆች ደሞዝ በሁሉም መመዘኛዎች ዝቅተኛ የሚባል ሲሆን የሥራው ባህሪ አካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጫና ያለው ነው። የአስተናጋጆቹ አብዛኛው ገቢያቸው ከደንበኞች በሚተውላቸው ጉርሻ (ቲፕ) ላይ የተመሠረተ ነው። በመሆኑም በ2019ኙ የሠራተኛ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የደሞዝ መጠንን የሚወስንን አካል ማቋቋም፣ ለሠራተኞች እና ለቤተሰቦቻቸው የተሻለ ህይወትን ለመፍጠር፣ እና ሠራተኞች (ሴት አስተናጋጆች) ህይወታቸውን እንዲያሻሽሉ ለማነሳሳት የሚረዳ ወሳኝ እርምጃ መሆኑን ጥናቱ ይመክራል።

ጥላሁን ግርማ (ዶ/ር)
እና
ትግስት ታረቀኝ

ምንጭ፡- The State and Transformation of Female Wage Labour in Ethiopia: Lessons from the Textile/ Garment, Floriculture and Hospitality Industries. Ezana Amdework and Belete Bizuneh (Ed).

ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ ሠነድ የታተመው ከኦፕን ሶሳይቲ ኢንሽየቲቭ (ኦሶኢ) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡ ለሠነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የተመራማሪዎቹ ሲሆን በምንም ሁኔታ የለጋሽ ድርጅቱን ወይም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስን አቋም እንደሚያንጸባርቅ ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡

§§ አድራሻ፡- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) §§ ፖ.ሣ.ቁ.፡- 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

§§ ስልክ፡- 0111545605/06 §§ ፋክስ፡- 0111545608 §§ ኢሜል፡- fss@ethionet.et §§ ድረ-ገጽ፡- www.fssethiopia.org